# የዋጋ ንረቱን ለመቋቋም የተወሰዱ ውጤታማ ክንዋኔዎች

ህይወት ፈለቀ 09/14/13

ከጥቂት ዓመታት ወዲህ በገበያው ላይ የተፈጠረው የዋጋ አለመረጋጋትን ጉዳዩ ያላለው ወገን አለ ብዬ አልገምትም፡፡ ሁኔታው ለብዙሃኑ ሕዝብ ዱብ ዕዳ ነበር ለማለት ይቻላል። በተለይ ሸማቹን ህዝብ ከልብ ያሳዘነ መሆኑን እርግጠኛ ለመሆን ምስክር ማፈላለግ የሚጠይቅ አልመሰለኝም። መንግስትም ቢሆን ከሕዝቡ የተለየ አቋም አልነበረውም።

ይሁንና በችግሩ መከሰት እጅግ ከማዘኑ ባሻገር፤ የሚጠበቅበትን ሁሉ በማድረግ ገበያውን ለማረጋጋት ምላሹ ፈጣን ነበር። እዚህ ላይ በምርቶች ላይ በታየው የዋጋ ንረት የመንግስትና የህዝቡ ስሜትና ፍላጎት አንድና አንድ ነበር በምልበት ጊዜ፤ የችግሩ መፈጠር “ጮቤ” ያስረገጣቸው ኃይሎች ጥቂትም ቢሆኑም ጭርስኑ አልነበሩም እያልኩ ግን አይደለም፡፡ በገበያው ውስጥ ያጋጠመው ጊዜያዊ አለመረጋጋት አስቦርቋቸው የነበሩ ኃይሎች እነማን ናቸው? መሆናቸው ጉዳዩ ውሎ አድሮ ገሃድ ሲወጣ ያስተዋልነው ሃቅ ነው።

ስለ ኑሮ ውድነቱም ሆነ ችግሩን ለመፍታት ስለተወሰዱና እየተወሰዱ ስለሚገኙ እርምጃዎች በተሻለ መልኩ ለመገንዘብ ይረዳ ዘንድ በቅድሚያ የችግሩ መነሻ ምንድ ነበር? የሚለውን መመልከቱ ጠቃሚ ይሆናል፡፡ እንደሚታወቀው ሀገራችን በነጻ የገበያ ሥርዓት መመራት ከጀመረች ከሁለት አስርት ዓመታት በላይ ዕድሜን አስቆጥራለች፡፡ ይህም በሃገር ውስጥ ፈጣን፣ ዘላቂ፣ ተወዳዳሪና ከተፅእኖ የጸዳ የንግድ ስርዓት እንዲሰፍን ያስቻለ ነው።

ይህም ሸማቹም ሆነ አምራቹ ያለማንም ጣልቃ ገብነት የንግድ ልውውጡን እንዲያካሂዱ ሙሉ ነፃነት የሰጠ ስርአት ከመሆኑም ባሻገር፤ ልማታዊ ባለሃብትን በጥራትና በብዛት እንዲፈጠርም የማይተካ ሚና ተጫውቷል፤ በመጫወት ላይም ይገኛል። መንግስትም የነጻ ገበያ ሥርዓቱን ከመዘርጋት ጀምሮ ስር እንዲሰድ በማድረግ በኩል የአንበሳውን ድርሻ ይዞ ችግሩን በቁርጠኝነት እየተወጣ ይገኛል።

ይህ ከሆነ ታዲያ ‘ከቅርብ ጊዜያት ወዲህ የንግድ ሥርዓቱን ጤና ሊያውክ የሚችል ምን በሽታ ሊከሰት ቻለ?’የሚል ጥያቄ ማንሳት ያስፈልጋል። እርግጥ በሀገር ውስጥ ገበያ ላይ ለታየው

ያለመረጋጋት ችግር መነሻው የተለያየ ነበር፡፡ በተለይም ከዓለም አቀፍ  የገበያ ሁኔታ ጋር ተያይዞ የመጣው ተፅዕኖ ለችግሩ ዋነኛው ምክንያት ነበር ለማለት ይቻላል፡፡

በዓለም አቀፍ ደረጃ ፈጣንና ሰፊ የሆነ የገበያ ትስስር የተፈጠረበት ጊዜ ላይ የምንገኝ መሆኑ ይታወቃል፡፡ ትስስሩ በኢኮኖሚ የበለፀጉትን ብቻ ሳይሆን በማደግ ላይ የሚገኙ ብዙሃኑን የዓለም ሃገራት ያካትታል–አንድም ምርትን በመሸጥ አሊያም በመግዛት።

ኢትዮጵያም የዚሁ  አካል መሆኗን ያጠናከረችበት ደረጃ ላይ ትገኛለች። ከመቶ ሃያ ከማያንሱ ሀገራት ጋር የንግድ ልውውጥ በማድረግ ላይም ናት፡፡  በገበያው እንደ ቡና፣ የቅባት እህሎችና ሌሎች ለዓለም አቀፍ ገበያ የሚሆኑ ሀገራዊ ምርቶችን በመሸጥ ጠቀም ያለ የውጭ ምንዛሪ እያገኘች ስትሆን፤ በምትኩም እንደ ነዳጅን የመሳሰሉ ምርቶችን ለምታካሂዳቸው የልማት ስራዎች ወሳኝ ድርሻ ያላቸውን  ጥሬ ዕቃዎች ታስገባለች፡፡

ይህ እንደ ሌሎች ሀገራት ሁሉ ለሀገራችን ኢኮኖሚ ማደግ ትልቅ ፋይዳ ያለው ገበያ ፤በተለያዩ ምክንያቶች ከቅርብ ዓመታት ወዲህ ሊታመም ግድ ሆኖበታል፡፡ ይህም በተለያዩ ምርቶች ላይ ፈጣንና ያልተገመተ የዋጋ ጭማሪ እንዲከሰት ምክንያት ነበር። ሃገራችን ከውጭ የምታስገባቸው እንደ ነዳጅና ሌሎች የምርት ዓይነቶች ላይ የዋጋ ጭማሪ ሊፈጠር የቻለውም ከዚሁ በመነጨ ምክንያት ነው፡፡

በወቅቱ በሀገር ውስጥ ገበያ ላይ የአንዳንድ ምርቶች ዋጋ መናር ትልቁ መንስዔ ከዓለም አቀፉ የገበያ ሁኔታ ጋር ሊያያዝ የሚችል ቢሆንም፤ ለችግሩ ሌሎች ተጨማሪ መነሻዎችም ነበሩት። ከእነዚህ ውስጥ አንዱ በሀገሪቱ ልዩ ልዩ አካባቢዎች እየተፋጠኑ ከሚገኙ የልማት ስራዎች ጋር  በተያያዘ የአንዳንድ የምርት ዓይነቶች ተፈላጊነት መጨመር ነው፡፡

በእርግጥ ይህ በልማቱ ምክንያት የሚፈጠር የዋጋ ጭማሪ የማይገመትና እንደ ከባድ ችግር የሚቆጠር አይደለም፡፡ ልማት እስካለ ድረስ የአንዳንድ ምርቶች አስፈላጊነት መጨመሩም አይቀሬ ነው፡፡

ይህ እስከሆነም ደግሞ አምራቹ በእነዚህ  የምርት ዓይነቶች ላይ ምክንያታዊ የሆነ ጭማሪ ሊያደርግባቸው የሚችልበት አጋጣሚ ሊፈጠር ይችላል፤ የነጻ ገበያ ሥርዓቱን የሚፃረር

አይደለምና፡፡ እንደ ሲሚንቶ፣ ብረታ ብረት፣ የቅባትና አንዳንድ የጥራ ጥሬ እህሎች ላይ የታየው ጭማሪም ከዚህ አኳያ በማሳያነት ሊቀርብ የሚችሉ ናቸው፡፡

ለገበያው አለመረጋጋት አደገኛው መንስዔ ተደርጎ ሊታይ የሚችለው ሌላው ነገር ደግሞ በነጋዴው ውስጥ በመሸጉ ኪራይ ሰብሳቢዎች ምክንያት የደረሰው ነው፡፡ በጽሑፌ መግቢያ ላይ በችግሩ መፈጠር ጮቤ የረገጡ ጥቂት ኃይሎች ነበሩ ብዬ ያስቀመጥኩት ዕውነታ እነዚህን ወገኖች ይመለከታል፡፡

እንደሚታወሰው በንግድ ሥርዓቱ ላይ ያለመረጋጋት ችግር መታየት በጀመረበት ወቅት በሁሉም የምርት ዓይነቶች ላይ የተከሰተ የዋጋ ንረት አልነበረም፡፡ ሊከሰትም አይችልም ነበር። ነዳጅን ጨምሮ ከውጭ የሚገቡ የተወሰኑ የምርት ዓይነቶች ላይ ብቻ ነበር ጭማሪው የተስተዋለው፡፡ ይህ በቂ ምክንያት ያለው በመሆኑ ህዝቡ ለመቀበል ብዙም አላንገራገረም።

መንግስትም ቢሆን በዓለም አቀፉ ገበያ መታወክም ሆነ በልማቱ ምክንያት የተፈጠሩት ጊዜያዊ ተጽዕኖዎች ሕዝብን የሚጎዱ አይደሉም ብሎ እጁን አጣጥፎ አልተቀመጠም፡፡ የነጻ ገበያ ሥርዓቱን የማያስተጓጉል ፈጣን ውሳኔ የመውሰድ እርምጃ ነበር ያደረገው፡፡ በወቅቱ በነዳጅና በግንባታ ጥሬ ዕቃዎች ላይ የተፈጠረውን የገበያ አለመረጋጋት ለማስተካከል መንግስት ከካዝናው በመደጎም ወደሃገር ውስጥ እንዲገቡ ከማድረጉም በተጨማሪ፣ አንዳንድ ምርቶችም ከቀረጥ ነጻ እንዲገቡ የፈቀደበት ሁኔታ እንደነበር የሚዘነጋ አይደለም፡፡

መንግስት ከራሱ ካዝና ደጉሞም ይሁን ከቀረጥ ነጻ እንዲገቡ በመፍቀድ የገበያ ሁኔታውን ለማረጋጋት ያደረጋቸው ጥረቶች በመንግስት በጀትና ገቢ ላይ ቀላል የማይባል ተጽዕኖ እንዳለው አያጠያይቅም። ግና መንግስት እነዚህ ተፅእኖዎች እንዳሉ እየተገነዘበም ቢሆን እርምጃውን ከመውሰድ ወደኋላ አላለም ነበር። ይህ ደግሞ የመንግስትን ሩቅ አሳቢነት አጉልቶ የሚያሳየን ሃቅ ነው፡፡

መንግስት ለጊዜያዊው ችግር መፍትሄ ያላቸውን እርምጃዎች በመውሰዱ በገበያው ውስጥ እፎይታ ሊፈጠር ችሎ ነበር። ይሁን እንጂ፣ መንግስት ችግሩን ለማቃለል በሚረባረብበት ወቅት ከመንግስት አስተሳሰብ በተቃራኒው የቆሙ ስግብግብ ኃይሎች በችግሩ ላይ ነዳጅ ለማርከፍከፍ ከመረባረብ አልቦዘኑም። በእርግጥ እነዚህ ኃይሎች ጥቂቶች ሊባሉ የሚችሉ ናቸው፡፡ ሊያደርሱ ከሚችሉት ጥፋት አንጻር ሲመዘኑ ግን ቀላል ግምት የሚሰጣቸው አይደሉም፡፡

ጠንካራ የፋይናንስ አቅም ያላቸው ከመሆናቸው ባሻገር፤ በገበያው ውስጥ ስር የሰደደ ትስስርም የነበራቸው ናቸው፡፡ እነዚህ አቅሞቻቸውን በማስተባበርም ከፍተኛ ጥፋት ለማስከተል መረባረባቸውን ደግሞ በገሃድ ያስተዋልነው ነው፡፡ በአንድ በኩል ምርቶችን በመደበቅ በገበያ ውስጥ እጥረት እንዲከሰት ያደረጉበት ሁኔታ የነበረ ሲሆን፤ በሌላም በኩል ደግሞ ልማታዊ ነጋዴው በሚያዋጣው ዋጋ እንዳይሸጥ ተፅዕኖ ለመፍጠር መጠነ ሰፊ ዘመቻም አካሂደዋል፡፡

እነዚህ ኪራይ ሰብሳቢዎች የዘረጉት የጥፋት መዋቅር በአዲስ አበባ አሊያም በጥቂት የክልል አካባቢዎች ብቻ የታጠረ አልነበረም፡፡ እስከ አርሶ አደሩ ድረስ ዘልቆ በመግባት ተፅዕኖ ለማድረስም ተንቀሳቅሰዋል፡፡ አርሶ አደሩ ምርቱን ወደ ገበያ እንዳይወጣ የሃሰት ፕሮፓጋንዳን በመንዛት፣ ነጋዴውም ምርቱን እንዲሰውርና አጋጣሚውንም ተጠቅሞ ከግብር ነጻ ነኝ ብሎ እንዲገምት ውስጥ ለውስጥ ቅስቀሳ ያካሄዱበት ሁኔታም ነበር፡፡

ይህ ነው እንግዲህ ምክንያታዊ በሆኑትም ባልሆኑትም የምርት ዓይነቶች ላይ የዋጋ ንረት እንዲመጣ ትልቅ ተጽዕኖ ሊፈጥር የቻለው፡፡ ምርቱ ሰፈር ውስጥ እየተመረተ፤ ከበቂ በላይ እንዳለ በምናስተውላቸው የምርት ዓይነቶች ሳይቀር ከነዳጅና ከሌሎች መሰል ጥሬ ቃዎች ጋር እኩል ዋጋቸው አልቀመስ የማለቱ ችግርም ከሌላ ምክንያት የሚመነጭ ሳይሆን፤ እነዚህ ኃይሎች በወጁት የሥነ - ልቦና ጦርነት ምርኮኛው በመብዛቱ ነው ለማለት ይቀላል፡፡

እነዚህ ስግብግብ ኃይሎች በዘረጉትና በሌሎች ምክንያቶች የተፈጠረው የገበያ አለመረጋጋት ዞሮ ዞሮ የሚጎዳው ህዝብን ነው፡፡ ይህ መሆኑ ግልፅ እስከሆነም ድርስ መንግስት ህዝብን ከችግር ውስጥ የማውጣት ግዴታውን ለመወጣት መረባረብ የግድ ይለዋል፡፡ የመንግስት እርምጃም ይህ ነበር። በገበያ ውስጥ የተፈጠረው ጊዜያዊ አለመረጋጋት እየተባባሰ ከመሄዱ በፊት የነጻ ገበያ ሥርዓቱን በማይጎዳ መልኩ የህዝብን ችግር ለመፍታት የሚያስችሉ ልዩ ልዩ አማራጮችን በመፈተሽ እርምጃ ወደመውሰድ ሊሸጋገር ችሏል፡፡

ለመንግስት ሠራተኞች ደሞወዝ የጨመረበት፣ በመሰረታዊ ሸቀጦች ላይ ጊዜያዊ ተመን ያወጣበት፣ ህገ - ወጥ ነጋዴዎች ከሠላማዊ የገበያ ሥርዓቱ የመነጠልና እርምጃ የመውሰድ፣ ወዘተ. ተግባሮችን በዋቢነት ይጠቀሳሉ፡፡ መንግስት የዋጋ ንረቱን ለመከላከል የወሰዳቸው እርምጃዎችና ያከናወናቸው ተግባሮች ባለፉት ጊዜያት በነበሩት ሁኔታዎች ብቻ የሚገለጹና የሚያበቁም አይደሉም፡፡ ከላይ ለማሳያነት የተጠቀሱት መንግስታዊ ተግባራቶች ህዝቡ በዋጋ ንረቱ ከፍተኛ

ጉዳት እንዳይደርስበት ትልቅ ዕገዛ እንዳደረጉ ቢታመንም፤ ዘላቂነት ያለው መፍትሄ እንዳልሆኑ ይታወቃል፡፡ የዋጋ ንረቱን ቀጣይነትና ዘላቂነት ባለው ሁኔታ ለማስወገድ ከፍተኛ ድርሻ በሚኖራቸው ጉዳዮች ዙሪያ ትኩረት ሰጥቶ ርብርቡን አጠናክሮ መቀጠል የሚገባ መሆኑም አጠያያቂ አይደለም፡፡

ማንም የዚህ ፅሁፍ አንባቢ እንደሚገነዘበው፤ በልማት መፋጠን ምክንያት ሊመጡ የሚችሉ የፍላጎቶችም ሆነ የዋጋ መጨመር ዋናውና ዘላቂው መፍትሄ  ልማቱን ማፋጠን ነው፡፡ መንግስትም ይህንኑ ሃቅ በጥልቀት ተገንዝቦ ለተፈጠረው ጊዜያዊ የገበያ አለመረጋጋት ዘላቂ መፍትሄ ሊሰጡ የሚችሉ የልማት ስራዎችን ማፋጠኑን ቀጥሏል፡፡

ለአብነት ያህል የአስሩም ስኳር ፋብሪካዎች ግንባታ በከፍተኛ ሁኔታ እየተካሄደ ያለ ሲሆን፤ ፋብሪካዎቹ በሙሉ አቅማቸው ወደምርት ተግባር ሲሸጋገሩ የስኳር ችግርን በአስተማማኝ ደረጃ ማስወገዳቸው አይቀሬ ነው፡፡ በሌላም በኩል መንግስት ምርትና ምርታማነትን በማሳደግ የገበያውን ሁኔታ የተረጋጋና የተሳለጠ እንዲሆን ያደረገው ጥረትም የተሳካ ውጤት እያስገኘ ነው፡፡ ለዚህም መንግስት በተከተለው ስትራቴጂ የግብርናውን መስክ ውጤታማነት ከአምናው ተመሳሳይ ወቅት በላቀ ሁኔታ እንዲጨምር በማድረጉ፤ ለሀገሪቱ ኢኮኖሚያዊ እድገት እንዲሁም የዋጋ ንረት ለማስተካከል ከፍተኛ ሚና እንዳለው ተገንዝቦ ተግባራዊ  እርምጃዎችን መውሰዱ የጠቃሽ ነው፡፡

በዚህም አርሶ አደሩ በ2004 የምርት ዓመት የተሻለ ምርት እንዲሰበስብ የተለያዩ ድጋፎችን ሲያደርግ ቆይቷል። ለምሳሌ ያህል አርሶ አደሩ የምርጥ ዘር፣ የማዳበሪያና ወዘተ. አቅርቦቶችን በወቅቱ በበቂ ሁኔታ አግኝቶ ወደ ምርት ተግባሩ እንዲገባ መንግስት ከፍተኛ ተግባር ፈፅሟል። በተጨማሪም ለአርሶ አደሩ ልዩ ልዩ የቴክኒክ ድጋፎችን በመስጠት በኩል ውጤታማ ስራዎችን ሊያከናውን ችሏል፡፡ በዚህም ሁኔታ በምርት ዘመኑ ወቅት በግብርናው መስክ ከፍተኛ የሆነ ውጤት ለመዘገብ የቻለበት ሁኔታ ሊፈጠር በቅቷል፡፡ በዘንድሮው የምርት ዓመት ከ220 ሚሊዮን ኩንታል በላይ ምርት እንደሚገኝ የተገመተ ሲሆን፤ ይህም ከአምናው ተመሳሳይ ወቅት ጋር ሲነጻጸር የ15 ሚሊዮን ኩንታል ምርት ብልጫ አለው፡፡

በዘንድሮ ዓመት በግብርናው መስክ የታየው ውጤት በገበያው ውስጥ በተለይም በግብርና ምርቶች ላይ ይስተዋል የነበረውን የዋጋ ጭማሪ ከማረጋጋት አንጻር ከፍተኛ ትርጉም እንዳለው

አያጠያይቅም፡፡ በመሆኑም በዚህ መልኩ ተፈጥሮ የነበረው የዋጋ ንረት በውስን ጊዜያት ውስጥ ይረግባል ተብሎ ይጠበቃል፡፡ እዚህ ላይ ከወዲሁ እየተባለ ስላለ አንድ ጉዳይ አይቶ ማለፍ ጠቃሚ ይሆናል፡፡ ይህም በዘንድሮ ዓመት የግብርናው ምርት ከፍተኛ ከመሆኑ ጋር ተያይዞ አርሶአደሩ ገበያው የሞትበታል በሚል ከወዲሁ በአንዳንድ ወገኖች እየተንጸባረቀ ያለው ስጋት ነው፡፡ በእርግጥም ቀደም ሲል በአርሶ አደሮች አካባቢ የነበረው ተሞክሮ ይህንን ስጋት የሚጭር በመሆኑ አስተሳሰቡ ፍጹም ያልተጠበቀ አሊያም ባዕድ ነው የሚባል አይደለም፡፡

ዳሩ ግን አሁን በተጨባጭ ባለው ሁኔታ አርሶ አደሩ ምርቱ በተትረፈረፈበት ወቅት እጁ ሰባራ፣ ምርቱ በጠፋበት ጊዜ ደግሞ ለእርዳታ እየተዳረገ የሚኖርበት አጋጣሚ አይኖርም– መንግስት አርሶ አደሩ ምርቱን የሚሸጥበት ምቹ የገበያ ሁኔታ ፈጥሯልና፡፡ ይህ ሰፊ የገበያ አጋጣሚም አርሶ አደሩ የልፋቱን እንዲያገኝ የሚያስችለው በመሆኑ፣ የምርቱ መጨመር 'ገበያው ይወርድብኛል' ብሎ የሚሰጋበት ሁኔታ እንዳይኖር ያደርጋል፡፡ ቀደም ሲል ከነበረው ተሞክሮ ለመገንዘብ እንደሚቻለው፣ የአርሶ አደሩ ምርት መጨመር የሚያሰጋቸው አንዳንድ ወገኖች፣ የምርቱ መቀነስ አርሶ አደሩን ትርፋማ እንደሚያደርግ ግንዛቤው ያላቸው አይደሉም፡፡ ምክንያቱም ቀድሞውንም ቢሆን አርሶ አደሩ ምርት የለም በሚል ምክንያታዊ ያልሆነ ዋጋ ሲቆልል የተስተዋለበት አጋጣሚ አልነበረም፡፡

ይልቁንም ከአርሶ አደሩ ተረክበው ለሸማቹ ህብረተሰብ የሚያቀርቡ ጥቂት ህገ-ወጥ ነጋዴዎች የሚፈጥሩት ተፅዕኖ በገበያው ላይ ችግር እየፈጠረ የነበረበት ሁኔታ መኖሩ በገሃድ ተስተውሏል፡፡ እናም የምርት መጨመር የአርሶ አደሩን ገበያ ይጎዳል የሚለው አስተሳሰብ ከወዲሁ ሊቀጭ ይገባዋል፡፡ መንግስት የዋጋ ንረቱን ለማስተካከል በተለይም በዘንድሮው ዓመት እየወሰዳቸው ከሚገኙት እርምጃዎችና ተግባራት መካከል የብድር ስርዓቱን የመቆጣጠርም ተጠቃሽ ነው፡፡ እንደሚታወቀው በገበያው ውስጥ ከፍተኛ ገንዘብ መሰራጨቱ የዋጋ ንረትን ሊያስከትል ይችላል፡፡

ከዚህም አንጻር መንግስት በገበያው ውስጥ የተፈጠረውን ችግር ለማቃለል ባለፈው ዓመት የተለየያ ድጎማዎችን ሲያደርግ ቆይቷል፡፡ ለተጀመሩ የልማት ስራዎች ወሳኝ የሆኑ ጥሬ ቃዎችን ከውጭ ለማስገባት የሚያደርገውን እንቅስቃሴ አስተማማኝ ደረጃ ከፍ ለማድረግ ከፍተኛ የሆነ የዶላር ግዢም ሲያደርግ ቆይቷል፡፡ በተለያዩ የኢንቨስትመንት መስክ ላይ ለሚሰማሩ ባለሃብቶችም ከፍተኛ ብድር ሲሰጥ የነበረበት አጋጣሚም ነበር፡፡

በእነዚህና መሰል ጉዳዮች መንግስት ባለፈው ዓመት ከብሔራዊ ባንክ ከፍተኛ ገንዘብ የተበደረበት ሁኔታ ተፈጥሯል፡፡ ይህ ደግሞ በገበያው ውስጥ ከፍተኛ የሆነ የገንዘብ ስርጭት እንዲኖር ዓይነተኛ ተፅዕኖ አሳርፏል፡፡ በመሆኑም በዘንድሮ ዓመት መንግስት የብድር ስርዓቱን ለመቆጣጠር ዕቅድ ነድፎ ወደ ተግባራዊ እርምጃ ተሸጋግሯል፡፡ በዚህም መሰረት መንግስት በዘንድሮ ዓመት ከብሔራዊ ባንክ ብድር የማይወስድ ይሆናል፡፡ በኢንቨስትመንቱ መስክ ላይ ለተሰማሩ ባለሃብቶች የሚሰጠው ብድርም የገንዘብ ስርጭትን የሚያባብስ እንዳይሆን የቁጥጥር ስራ ተፈጻሚ የሚደረግ ነው የሚሆነው፡፡

ሌላው መንስት የዋጋ ንረትን ለመቆጣጠር እየወሰደ የሚገኘው እርምጃ የዶላር ሽያጭን ማካሄድ ነው፡፡ ቀደም ሲል ለመጠቆም እንደሞከርኩት፣ መንግስት ባለፉት ጊዜያት የልማት ሥራዎችን ለማፋጠን ከፍተኛ የሆነ የዶላር ክምችት ፈጥሯል፡፡ ይህም በአሁኑ ወቅት የዶላር ችግር እንዳይኖረው አድርጓል። በዘንድሮ ዓመት የዋጋ ንረቱን ለመቆጣጠር በመንግስት እየተወሰዱ ካሉት እርምጃዎች አንዱም ይህን የዶላር ክምችት ሽያጭ ማካሄድ ነው፡፡ ከዚህም አንጻር መንግስት ከፍተኛ የዶላር ሽያጭ በማከናወን ላይ ሲሆን፣ ቀደም ሲል ለትላልቅ ባለሃብቶች እና ለተወሰኑ የምርት ዓይነቶች ብቻ ይውል የነበረው የዶላር ግብይት፣ በአሁኑ ወቅት ማንኛውም ዜጋ ለመፈጸም እንዲችል ሁኔታዎችን አመቻችቷል፡፡

በመሆኑም ቀደም ሲል ግዙፍ የሆኑ ምርቶችን ለሚያስገቡ አስመጪዎች እንዲያገኙ የሚደረገው የዶላር ግዢ አገልግሎት፣ ዛሬ ላይ ጥቃቅን የሚባሉ የምርት ዓይነቶችን የሚያስገቡ አስመጪዎችም እንዲያገኙ እየተደረገ ነው፡፡ ከዚህ በተጨማሪም ዶላር ለመግዛት ጥያቄ የሚያቀርብ ዜጋ ሁሉ ዕድሉን በማግኘት ላይ ይገኛል፡፡ በድምሩ መንግስት የዋጋ ንረትን ለመከላከል ባለፉት ጊዜያት ልዩ ልዩ ጠቃሚ እርምጃዎችን በመውሰድ ህዝብ ተኮር ተግባራትን ሲያከናውን ቆይቷል፡፡ እነዚህ እርምጃዎችና ተግባራት ንረቱ በዜጎች ህይወት ላይ ጫና እንዳያስከትል አስተዋጽኦ የነበራቸው መሆኑ አይካድም፡፡

ይህ እንደተጠበቀ ሆኖ፣ መንግስት በዘንድሮ ዓመት ምርታማነትን በማሳደግ፣ የብድር ሥርዓቱን በመቆጣጠር፣ ከፍተኛ የዶላር ሽያጭ በማካሄድና ሌሎች የልማት ስራዎችን በማፋጠን ንረቱን በዘላቂነት ለመቆጣጠር ወሳኝ እርምጃዎችን በመውሰድ ላይ ይገኛል፡፡ እስቲ እነዚህ ተግባራት ከኢንዱስትሪው ዕድገት አኳያ የሚያመጡትን እመርታ እንመልከት።

እርግጥ ኢትዮጵያ በኢንዱስትሪ የበለፀገች ሀገር እንድትሆን ከተፈለገ ምርትና ምርታማነትን ማሳደግ፣ በምርጥ ዘርና ማዳበሪያ አቅርቦት ራስን መቻል የግድ መሆኑ አጠያያቂ አይደለም፡፡ እስካሁን ባለው ሂደት ለግብርና ግብአት የሆነውን ዩሪያና ዳፕ ማዳበሪያዎችን ከውጭ ሀገር እየገዛን እናስገባለን፡፡ ለአብነት ያህልም ከ2003 ዓ.ም ጀምሮ እስከ የአምስት ዓመቱ የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ መጨረሻ ድረስ ከአንድ ሚልዮን ቶን የሚልቅ ማዳበሪያ ያስፈልገናል። ፍላጎቱ ደግሞ እያደገ የሚሄድ ነው፡፡ ለዚህን ያህል ማዳበሪያ የሚወጣውን የውጭ ምንዛሪ ስናስብ ደግሞ መፍትሔ መሻት የግድ ይላል፡፡

መንግስትም ለማዳበሪያ ግዢ የሚወጣውን የውጭ ምንዛሪ ለማስቀረት የማዳበሪያ ፋብሪካ መገንባት አማራጭ የሌለው መፍትሔ መሆኑን ከግምት ውስጥ በማስገባት እንቅስቃሴ ጀምሯል፡፡ በዚህ መሠረት በኢንዱስትሪ ሚኒስቴር ባለቤትነት አምስት የዩሪያና ሦስት የዳፕ ማዳበሪያ ፋብሪካዎች ግንባታ በኦሮሚያ ክልል ተጀምሯል፡፡ ግንባታውን የሚያከናውነው የብረታብረትና ኢንጂነሪንግ ኮርፖሬሽን መሆኑ ደግሞ የውጭ ምንዛሬን በማስቀረት ረገድ የሚኖረው አስተዋፅኦ ሳይታለም የተፈታ ጉዳት ነው–"የሀገሩን በሬ በሀገሩ ሰርዶ" እንዲል የሀገራችን ሰው።

ፋብሪካዎቹ ግንባታቸው ተጠናቆ በሙሉ አቅማቸው ማምረት ሲጀምሩ የአርሶ አደሩን የግብአት አቅርቦት ችግር በመቅረፍ ለዚሁ ግዢ ይወጣ የነበረውን የውጭ ምንዛሪ ለማስቀረትና ለዜጐች የስራ እድል በመፍጠር ረገድ የማይተካ ሚና ይጫወታሉ፡፡ በኢንዱስትሪ የበለፀገች ኢትዮጵያን ለመፍጠርም መደላድል ይፈጥራሉ፡፡ በሂደት ደግሞ አቅምን አጐልብቶ ወደ ውጭ በመላክ የውጭ ምንዛሪ ገቢን ለማስገኘት የሚችልበትን እድል መፍጠራቸው አይቀሬ ነው፡፡

በዚህ መሰረት የኢንዱስትሪ ዞኖች ተለይተዋል፡፡ በዞኖቹ መሰረተ ልማቶችን አመቺ በሆነ መልኩ ለማሟላት ጥረት ተደርጓል፣እየተደረገም ነው፡፡ ከዚህ መሳ ለመሳም በኢንዱስትሪው መስክ የተሰማሩ የግል ባለሀብቶች የሚያመርቱት ምርቶች ጥራታቸው የጠበቁ እንዲሆኑ በብዛት ማምረት እንዲችሉ ድጋፍ እየተደረገላቸው ይገኛል፡፡ በዓለም አቀፍ ደረጃ ተወዳዳሪ እንዲሆኑም ጥረቱ ቀጥሏል፡፡

በዚህ ዘመን በዓለም ገበያ ተወዳድሮ ማሸነፍና ጥራት ያለውን ምርት ማምረት የግድ ይላል፡፡ በዚህ ጉዳይ ላይ ጠቅላይ ሚኒስትር መለስ “በዘመነ ግሎባላይዜሽን ለመቆም መሮጥ ያስፈልጋል፡፡ ለአፍታም ቢሆን መዝናናትና ማንቀላፋት የማይፈቅድ ስርዓት ነው፡፡ በአሁኑ ወቅት ከፊት የነበሩ ሀገሮች ወደ ኋላ እየተመለሱ ነው” ማለታቸው ይታወሳል። በአንጻሩ ከኋላ የነበሩ ሀገሮች ወደ ፊት በመገስገስ ላይ እንደሚገኙና በዚህ የሽግግር ጊዜ ድርሻን ማሻሻል ከተፈለገ 24 ሰዓት በተጠንቀቅ መቆምን፣ በውድድር ማሸነፍን ሌት ተቀን የመወዳደር አቅምን ማሻሻል እንደሚጠይቅም በማያሻማ ሁኔታ ገልፀው ነበር፡፡

እናም የታላቁ መሪያችንን በኢንዱስትሪ የበለጸገች ኢትዮጵያን የመፍጠር ራዕይ ለማሳካት ከመቼውም ጊዜ በላይ ጠንክሮ መስራት የሚያስፈልግበት ወቅት ላይ እንገኛለን፡፡ በመሆኑም በዓለማችን ካለው ተጨባጭ ሁኔታ አንጻር የግል ባለሀብቱ የተወዳዳሪነት አቅሙን መሻሻል ይጠበቅበታል፡፡ ባለሃብቱን ለመደገፍም መንግስትም ኢንዱስትሪው የሚፈልገውን የተማረ የሰው ኃይል ማፍራት ስራውን በስፋት ቀጥሎበታል፡፡ በመልካም አስተዳደር በኩልም የሚያጋጥሙ ችግሮችን የሚያቃልሉ ርምጃዎችን በመውሰድ ላይ ይገኛል፡፡ በኢንዱስትሪው መስክ የተሰማሩ ባለሀብቶች መዋቅራዊ ለውጥ ለማምጣት በሚደረገው ጥረት ጉልህ ስፍራ አላቸው።

ባለሃብቶቹም ይህንኑ ከግምት ውስጥ በማስገባት የመንግስትን ጥሪ ተቀብለው የበኩላቸውን አስተዋጽኦ በማበርከት ላይ ናቸው፡፡ ከግብርና መር ኢኮኖሚ ወደ ኢንዱስትሪ መር ኢኮኖሚ የሚደረገው ሽግግርም በመንግስትና በእነርሱ የላቀ ተሳትፎ በትክክለኛው መስመር እየተጓዘ ነው፡፡ ነገ በምናያት በኢንዱስትሪ የበለፀገች ኢትዮጵያ ውስጥ ግንባር ቀደም ተዋናይ መሆናቸው ከአሁኑ በመታየት ላይ የሚገኘው በሺዎች የሚቆጠሩ የከተማ ነዋሪዎች በዘርፉ ተሰማርተው የተሳካና ውጤታማ ስራ በማከናወን ላይ ይገኛሉ፡፡

በያዝነው የአምስት ዓመት ዕቅድ መጠናቀቅ በኋላ ከግብርና መሪ ወደ ኢንዱስትሪ ወደ ህብረተሰብ እንድትሸጋገር የሚያስችል ሁኔታ ለመፍጠር መንግስትና በግሉ ሴክተር የሚከናወኑ የኢንዱስትሪ ልማት ፕሮጀክቶችን ሲያስፋፋ ቆይቷል፡፡ በመሆኑም የግሉ ሴክተር ከሚያደርጋቸው ትላልቅ ልማታዊ ስምሪቶች ጐን ለጐን በመንግስት ልማት

ድርጅቶች የተለያዩ የኢንዱስትሪ ልማት ፕሮጀክቶች እንዲከናወኑ እየተደረገ ይገኛል፡፡ ከነዚህ መካከል ስራቸው ተጀምሮ በመፋጠን ላይ ያሉት አስር የስኳርና አንድ የማዳበሪያ ማምረቻ ፋብሪካ ይገኙበታል፡፡

መንግስት በተለይ የስኳር ፋብሪካዎችን በሀገራችን አቅም የመስራት ልምድ እንድናዳብርና ፋብሪካዎችን የመገንባት አገራዊ አቅም እንዲኖረን በማሰብ በሚያካሂደው ልማት ሁሉም ስራዎች በተቀመጠላቸው አቅጣጫ እየተፈፀሙ ይገኛሉ፡፡ በመሆኑም ወደ ኢንዱስትሪ የሚደረገው ጉዞ በትክክለኛ መንገድ ላይ ይገኛል ለማለት ያስደፍራል፡፡ እናም መጪው ጊዜ የኢንዱስትሪ ዘመን መሆኑን የሚያመላክቱ ተግባራት ባለፉት ሁለት የዕድገትና የትራንስፎርሜሽን ተፈፃሚ መሆናቸው ህዳሴያችንን ቅርብ መሆኑን አመላካች ናቸው።

እነዚህ ሁኔታዎችም ምርቶች በሀገር ውስጥ እየተመረቱ የውጭ ምንዛሪን ስለሚቀንስ የዋጋ ንረቱንም በዚያኑ መጠን እንዲቀንስ ያደርጉታል። ይህም በህብረተሱ ውስጥ ሊኖር የሚችለውን የኑሮ ክብደት በመቀነስ ረገድ የማይተካ ሚና ይኖረዋል። የእያንዳንዱ ዜጋ የኑሮ ሁኔታ አሁን ካለው ይበልጥ ከተለወጠ ደግሞ ሀገራችን የተለመችውና መካከለኛ ገቢ ያለው የህብረተሰብ ክፍል መፈጠሩ አይቀሬ ነው። ታዲያ ተግባራቱ የዋጋ ንረቱ ዕድሚው ከወዲሁ አጭር እየሆነ የሚሄድ መሆኑን የሚያመላክቱ ናቸው ማለት ይቻላል፡፡ ይህም ለብዙሃኑ ህዝብ የምስራች ነው—ከዋጋ ንረቱ እፎይ ሊል ነውና። ከዚህ ጎን ለጎንም መንግስት ሁለት አሃዝ የነበረውን የዋጋ ንረት ወደ አንድ አሃዝ ሲያወርደው መረጋጋቱ የሚቀር አይመስለኝም።